# የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን

## መመሪያ ቁጥር 541/2013

## ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ቦርድ የሚቀርቡ የይግባኝ ጉዳዮች የሚስተናገዱበት ሥነ ሥርአት መመሪያ

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ቦርድ የአስተዳደር ችሎቱ ወሳኔ የሰጠባቸዉን ጉዳዮች፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወሳኔ የተሰጠባቸዉን የዲሲፕሊን ጉዳዮችን በይግባኝ እንደሚያይ የተደነገገ በመሆኑ፣

ቦርዱን ይህን ተግባሩን ለመወጣት ይችል ዘንድ አሠራሩን ወጥ፣ ግልፅና ቀልጣፋ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በማግኘቱ፣

በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 አንቀጽ10 እና 34 /2/ መሠረት ይህ የይግባኝ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ቦርድ የይግባኝ ሥነ ሥርአት መመሪያ ቁጥር 541/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ፤

2.1 "የሚጨረሻ ወሳኔ" ማለት ጉዳዩን በይግባኝ በሚያየው አካል ወሳኔ ካልሆነ በስተቀር በማናቸውም የሥነ ሥርአት ሕጎች አፈፃፀም ምክንያት ወሳኔ በሰጠው አካል ቀርቦ ሊታይ በማይችልበት ሁኔታ የተሰጠ ወሳኔ ነው፡፡

2.2 "የዲሲፕሊን ወሳኔ" ማለት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ ቁጥር 5/2002 መሠረት የምርት ገበያ አባላት በደንቡ አንቀጽ 15.2 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በተፈፀሙ ጥፋቶች ምክንያት በምርት ገበያው የግብይት አፈፃጸም ኮሚቴ ታይተው ለምርት ገበያው ቦርድ በይግባኝ እንዲቀርቡ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ቦርዱ የሚሰጠው ወሳኔ ነው፡፡

2.3 በዚህ መመሪያ ወስጥ በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴት ጾታንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ይግባኝ ስለመቅረብ

3. ይግባኝ ስለሚቀርብባቸው ጉዳዮች

3.1. የባለስልጣኑ አስተዳደር ችሎት በሚሰጣቸው ማናቸወም የሚጨረሻ ወሳኔዎች፣ እና

3.2. የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በሰጠው ማናቸወም የሚጨረሻ የዲሲፕሊን ወሳኔዎች ላይ፣ ይግባኝ ሊቀርብባቸው ይችላል፡፡

3.3. ሆኖም ቦርዱ በሚከተሉት ሁኔታዎች የሚቀርቡለትን የይግባኝ አቤቱታዎች አያይም፤

3.3.1. በአስተዳደር ችሎትውሳኔ የተሰጠባቸውና በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ማሰረት እንደገና ለአስተዳደር ችሎቱ ቀርበው ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮችን፣

3.3.2. በቀጠሮ አሰጣጥ፣ ባለጉዳዮቹ የሚከራከሩበትን ጥቅም በተመለከተ ለአንዱ ወይም ለሌላው የመወሰን ወጤቱን በሚያስከትሉ ትዕዛዞች፣ እንዲሁም የክርክሩን ሂደት በማሟራት በሚሰጡ ሌሎች ትዕዛዞች ወይም ብይኖች ላይ የሚቀርቡ ይግባኞች፡፡

4. የይግባኝ ማስታወቂያ ስለማስጠት

4.1. አስተዳደር ችሎት ወይም የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባሳለፈው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኝ ለማቅረብ የሚፈልግ ሲሆን የውሳኔ ግልባጭ በደረሰው 15 ቀናት ወስጥ ይግባኝ የሚጠይቅ መሆኑን የሚገልጽ ማመልከቻ አዘጋጅቶ ለችሎቱ ሪጅስትራር ማቅረብ አለበት፡፡

4.2. የወሳኔ ግልባጩ ለተከሳሽ የተላከው በፖስታ ቤት በኩል ከሆነ ወሳኔ የተሰጠበት ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬.፩. የተመለከተውን የይግባኝ ማስታወቂያ የመስጫ ጊዜ በሦስት ቀን ይራዘማል፡፡

4.3. የችሎቱ ሬጅስትራር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4.1. የተመለከተው ማስታወቂያ እንደደረሰው ይመዝግባል፤ ስለመመዝገቡም ለአመልካቹ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

4.4. ወሳኔው የተሰጠበት ሰው በዚህ አነቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4.1. የተመለከተወን ማስታወቂያ በሰጠ በ30 ቀናት ወስጥ የይግባኝ ማመልከቻውን አዘጋጅቶ ለቦርዱ ጽ/ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

4.5. የችሎቱ ሬጅስትራር በዚህ አንቀጽ 4.3. መሠረት የደረሰውን ማስታወቂያ ከማዝገበ በኋላ በተከታዩ ቀን ወይም እጅግ ቢዘገይ የይግባኝ ባዩ ማመልከቻ ለቦርዱ ጽ/ቤት በደረሰበት ቀን ይግባኝ የተጠየቀበትን የአስተዳደር ችሎት መዝገብ ወይም የመዝገቡን ትክክለኛ ግልባጭ በማሸኛ ለቦርዱ ማላክ አለበት፡፡

4.6. የይግባኝ ማመልከቻ ስለማቅረብ

4.6.1. ይግባኝ ጠያቂው የሚያቀርበው የይግባኝ ማመልከቻ የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዮች ይይዛል፡፡

/ሀ/ የተጻፈበትን ቀን፣

/ለ/ የቦርዱን ስም፣

/ሐ/ የይግባኝ ባይና የመልስ ሰጭን ስም፣

/መ/ ይግባኝ የተባለበት ወሳኔ የተሰጠበትን መዝገብ ቁጥር፣

/ሠ/ ለይግባኝ ማሰረት የሆነወን የአስተዳደር ችሎት ወሳኔ ይዘት በአጭሩ፣

/ረ/ ይግባኝ ባይ ወሳኔወን የሚቃወምባትን ምክንያትና የሚጠይቀውን ዳኝነት፣

/ሰ/ ይግባኝ ባይ ለይግባኙ አወሳሰን ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብለት የሚጠይቅ ሲሆን እንዲታይለት የሚጠይቀውን ማስረጃ ዝርዝርና እንዲሰሙለት የሚፈልጋቸውን ምስክሮች ስም የሚገልጽ ሌላ ጽሁፍ ከይግባኝ ማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

/ሸ/ ይግባኝ ባዩ እንዲታዩለት የሚጠይቃቸው ማስረጃዎች ወይም ይሰሙልኝ የሚላቸው ምስክሮች በአስተዳደር ችሎቱ ክርክር በተካሄደበት ወቅት ያልታዩ ወይም ያልተሰሙ ከሆኑ ሳይታዩ ወይም ሳይሰሙ የቀሩበትን በቂ ምክንያት እና አሁን የሚታዩበትን ወይም የሚሰሙበትን ምክንያት ዝርዝር መግለጽ አለበት፡፡

4.6.2. የይግባኝ ማመልከቻው በይግባኝ ባዩ ወይም በጠበቃው ወይም በሌላ ህጋዊ ወኪሉ ፊርማ ሚረጋገጥ ያለበት ሲሆን ይግባኝ ባዩ ህጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ሲሆን ከድርጅቱ ህጋዊ ወኪል ፊርማ በተጨማሪ የድርጅቱ ማህተም ያረፈበት መሆን አለበት፡፡

4.6.3. ይግባኝ ባይ ይግባኙን በሚያቀርብበት ወቅት ለመልስ ሰጭም የሚደርስ የይግባኝ ማመልከቻ ቅጂ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

5. የይግባኝ ማመልከቻን ስለመመዝገብ

5.1. የቦርዱ ጸሀፊ በአንቀጽ 4.4. መሠረት የቀረበው የይግባኝ ማመልከቻ የማቅረቢያ ጊዜው ሳያልፍ እና በተሟላ ሁኔታ የቀረበ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ይግባኙን መዝግቦ ቁጥር በመስጠት ፋይል ይከፍታል፡፡

5.2. የይግባኝ ማመልከቻው ያልተሟላ ከሆነ ተሟልቶ እንዲቀርብ ለአመልካቹ መመለስ አለበት፡፡

5.3. ለቦርዱ የሚቀርብ ማንኛውም ይግባኝ ወይም አቤቱታ የዳኝነት ገንዘብ አይጠየቅበትም፡ የውሳኔም ሆነ የማስረጃ ግልባጭ ለማግኘትም የሚከፈል ገንዘብ አይኖርም፡

6. መስቀለኛ ይግባኝ ስለማቅረብ

6.1. መልስ ሰጭው በቀጥታ ይግባኝ ያላቀረበ ቢሆንም እንኳን ይግባኝ ባዩ ባቀረበው የይግባኝ ክርክር በመልስ ሰጭነት ከሚያቀርበው ክርክር ጋር በፍርዱ ቅር የተሰኘበትን ጉዳይ በማቅረብ በይግባኝ ባይነትም ለመከራከር ይችላል፡፡

6.2. የመልስ ሰጭው የቅሬታ ማስሚያ አቤቱታ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4.6.1. መሠረት በይግባኝ ማስሚያ ማመልከቻ ፎርም ተዘጋጅቶ ለመልስ ሰጪው ወይም ለጠበቃው የመጥሪያ ትዕዛዝ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ ለቦርዱ መቅረብ አለበት፡፡

ክፍል ሦስት

ስለ ባለጉዳዩ ወደ ይግባኝ ሰሚው ቦርድ መቅረብና ሳይቀርብ መቅረት

7. ባለጉዳዩ ራሱ እንዲቀርብ አስፈላጊ ስለሚሆኑ፤

ለክርክሩ አወሳሰን የዋናው ባለጉዳይ መቅረብ ፍጹም አስፈላጊ የሚያደርግ በቂ ምክንያት ባጋጠመ ጊዜ ቦርዱ ባለጉዳዩ ራሱ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል፡፡

8. የመልስ ሰጪ ያለመቅረብ፤

ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀን ቀጠሮ ይግባኝ ባይ ቀርቦ መልስ ሰጪ ያልቀረበ እንደሆነ ለጉዳዩ ውሳኔ የሚሰጠው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ ነው፡፡

8.1. ለመልስ ሰጪ የተላከለት መጥሪያ የደረሰው መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ በሌለበት የነገሩ መስማት ይቀጥላል፡፡

8.2. መጥሪያው በትክክል መድረሱ ካልተረጋገጠ ቦርዱ ለሜሰ ሰጪ በድጋሚ መጥሪያ እንዲላክ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

8.3. መጥሪያው ያልደረሰው በይግባኝ ባዩ ቸልተኝነት ወይም ጉድለት መሆኑ ከተረጋገጠ የይግባኙ ማዘገብ እንዲዘጋ ሊወስን ይችላል፡፡

9. ስለተከራካሪ ወገኖች መቅረብ

9.1. ነገሩን ለማየት ቦርዱ በወሰነው ቀነ ቀጠሮ ይግባኝ ባይና ሜሰ ሰጪዎች ራሳቸው ወይም ወኪሎቻቸው ተሟልተው መቅረብ አለባቸው፡፡ የተከራካሪ ወገኖች መቅረብ እንደተረጋገጠ ክርክር ማሰማት ይጀምራል፡፡

9.2. ግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች በተወሰነው ቀጠሮ ሳይቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ቦርዱ ማዘገቡን ይዘገዋል፡፡

10. የይግባኝ ባይ ያለመቅረብ

ይግባኝ ባይ ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ እና ሜሰ ሰጪ ቀርቦ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ይግባኝ ባይ በሌለበትም ቢሆን ቦርዱ ውሳኔ ለማስጠት ይችላል፡፡ ሜሰ ሰጪው ክሱን የካደ እንደሆነ ግን ማዘገቡን በማዘጋት ሜሰ ሰጪ ያሰናብተዋል፡፡

11. የይግባኝ ማዘገብ ማዘጋት የሚያስከትለው ውጤት፤

11.1. ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች ማዘገቡ ከተዘጋ ይግባኝ ባይ በይግባኙ ክርክር ማንሻ የነበረውን ነገር ማስረት በማድረግ አዲስ ክስ ማቅረብ አይችልም፡፡ ሆኖም ይግባኝ ባይ ወይም ሜሰ ሰጪ ማዘገቡ በተዘጋ በበአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቦርዱን የሚያሳምን በቂ ምክንያት በማቅረብ እንደገና ተከፍቶ እንዲታይለት ሊጠይቅ የሚችልበትን መብት አያስቀርበትም፡፡

11.2. ቦርዱ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ይግባኝ ባይ ቀርቦ ለመከራከር ያልቻለው በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት መሆኑን የተረዳ እንደሆነ የተዘጋው ማዘገብ እንደገና ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል ለመወሰን ይችላል፡፡

12. ሜሰ ሰጪ በሌለበት እንዲታይ የተሰጠው ብይን ወይም ውሳኔ እንዲነሳለት ስለሚጠየቅበት ሁኔታ

12.1. ሜሰ ሰጪው ሜሰ እንዲሰጥ በተቀጠረበት ቀን ቀርቦ ሜሰ ሳያቀርብ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሳያቀርብ በመቅረቱ ክርክሩ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠ እንደሆነ ወይም በዚሁ ማስረት ታይቶ ውሳኔ የተሰጠ እንደሆነ ትዕዛዙ ወይም ውሳኔው ማስጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ በሌለበት እንዲታይ የተሰጠው ብይን ወይም ውሳኔ እንዲነሳለትና ክርክሩ እንደገና ባለበት እንዲቀጥል ሊያመለክት ይችላል፡፡

12.2. ሜሰ ሰጪው ጉዳዩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ለመቅረብ ወይም ቀርቦ መከራከሪያውን ለማቅረብ ያልቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑን የተረዳው እንደሆነ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተሰጥቶ የነበረውን ብይን ወይም ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ በማንሳት ክርክሩ እንደገና እንዲሰማ ለመወሰን ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## ይግባኝን ስለመመርመርና ውሳኔ ስለማስጠት

13. ቦርዱ ይግባኙን የሚመረምርበት አግባብ

13.1. ቦርዱ የይግባኝ ቅሬታውን የሚያየው አስተዳደር ችሎቱ ወይም ከምርት ገበያው ቦርድ የቀረበውን የጽሁፍና የቃል ክርክር እንዲሁም ማስረጃዎችና በችሎቱ የተመዘገቡ ትዕዛዞችና ውሳኔዎችን መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

13.2. ቦርዱ ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ የሚጠቅም ሆኖ ሲያገኘው በራሱ ተነሳሽነት ወይም በተከራካሪ ወገኖች በሚቀርብ አቤቱታ መሰረት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ሊያዝ ይችላል፡፡

14. የይግባኝ ማመልከቻን ስለ መመርመርና ክርክርን ስለማስማት

14.1. ለቦርዱ የቀረበ የይግባኝ ማመልከ ቻ ለቦርዱ ጉባኤ ቀርቦ እንዲታይ የሚደረገው ሶስት የቦርድ አባላት ጉዳዩን አይተው ሊጣራ የሚገባው የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ጭብጥ መኖሩን አምነው ሲወስኑ ነው፡፡

14.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ይግባኙን ለመመርመር የሚያስችል በቂ ምክንያት መኖሩ ከተወሰነ ቀጣዩ የክርክር ሂደት ቢያንስ በሶስት የቦርድ አባላት ይመራል፡፡

14.3. ሶስት የቦርድ አባላት የሚሰየሙበት ችሎት ጉዳዩን አይቶ የአስተዳደር ችሎቱን ወይም የምርት ገበያውን ቦርድ ውሳኔ የሚያስለውጥ በቂ ምክንያት አለመኖሩን ካመነበት መልስ ሰጪውን መጥራት ሳያስፈልግ ይግባኙን ወድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

14.4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ይግባኙን ለመመርመር የሚያስችል በቂ ምክንያት መኖሩ ከተወሰነ የይግባኝ ባይ ቅሬታ ለመልስ ሰጪው እንዲደርሰውና መልሱን እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

14.5. በቦርዱ የተሰጠው ትዕዛዝ ከይግባኝ ባይ የቅሬታ ማመልከቻ ጋር የቀጠሮው ቀን ከመድረሱ ከ አስር ቀን በፊት ለመልስ ሰጪ እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

14.6. መልስ ሰጪው ለቃል ክርክሩ ቀርቦ እንደሆነ የቃል ክርክሩን የሚጀምረው ይግባኝ ባይ ይሆናል፡፡ በመቀጠል መልስ ሰጪ ያስረዳል፡፡ በመጨረሻም የይግባኝ ማጠቃለያ ሀሳብ ይቀርባል፡፡

14.7. ቦርዱ በቃል ክርክር ወቅት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ሊፈቅድላቸው ይችላል፡፡

14.8. በቦርዱ ፊት የተደረጉት የቃል ክርክሮችና በማስረጃነት የቀረቡ ሰነዶች ዝርዝር ሁሉ በመዝገብ ላይ መስፈር አለበት፡፡

15. ስለቦርዱ ስልጣን

15.1. ቦርዱ በይግባኝ የተጠየቀውን ዳኝነት መሰረት በማድረግ በአስተዳደር ችሎት ወይም በምርት ገበያው ቦርድ የተሰጠውን ውሳኔ መሻር፤ ማሻሻል፣ ማጽናት፤ እንዲሁም ተጨማሪ ማጣራት የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች በመለየት ማስረጃ ሰምቶ እንደገና እንዲወስን ማዘዝ ይችላል፡፡

15.2. ቦርዱ በአስተዳደር ችሎቱ ወይም በምርት ገበያው ቦርድ የተሰጠው ውሳኔ ወዲያውኑ ተፈጻሚ ቢሆን በይግባኝ ባዩ ላይ ከፍ ያለና የማይመለስ ጉዳት ሊደርስበት የሚችል

መሆኑን ሲያምን ይግባኝ ባዩን ስለወሳኔው አፈጻጸም በቂ ዋስትና እንዲሰጥ በማድረግ ይግባኙ ወሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የአስተዳደር ችሎቱን ወሳኔ ለማገድ ይችላል፡፡

15.3. ቦርዱ የአስተዳደር ችሎቱ የሰጠው ወሳኔ እንዲታገድ የቀረበወን አቤቱታ የሚቀበለው ሲሆንና ይግባኙ ለይግባኝ ባዩ የሚወሰን ቢሆን ይግባኝ ባዩ ፍርዱን ለማስፈፀም የሚችልበት ሁኔታ በፈጠር ሊደርስ የሚችለወን ጉዳት ለማካገድ ሚልስ ሰጭው በአፈፃፀሙ ምክንያት የወሰደወን ንብረት ለማስመለስ ወይም ለማሸፈን የሚችል ገንዘብ እንዲያሲዝ ዋስትና እንዲሰጥ ለማዘዝ ይችላል፡፡

15.4. የቦርዱ ወሳኔ በተለየ ሁኔታ የሚፈጸም ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር በባለስልጣኑ ይፈጸማል፡፡ ወሳኔው የተለየ አፈጻጸም የሚፈረው ሆኖ ሲገኝ ቦርዱ ለአፈጻጸሙ ተገቢ ማሉ የሚሆየወን ትእዛዝ በማስጠት እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡

16. ስለቦርዱ ወሳኔ አሰጣጥ

16.1. ቦርዱ ወሳኔ የሚሰጠው ቢያንስ ሦስት የቦርድ አባላት ክርክሩን መርተው በሚቀርበት የወሳኔ ሀሳብ ላይ ተመስርቶ በአብላጫ ድምጽ ይሆናል፡፡

16.2. በማናቸወም ጊዜ ከአብላጫው ወሳኔ የተለየ ሀሳብ ያለው አባል የልዩነት ሀሳቡን ለይቶ ማስፈር ይችላል፡፡ ይህ የተለየ ሀሳብም ከአብላጫው ወሳኔ ሰነድ ሳይለያይ የሚሆይ የወሳኔው አካል ይሆናል፡፡

16.3. የቦርዱ ወሳኔ የሚሰጠው በጽሁፍ ሲሆን በሁሉም የቦርድ አባላት ይፈረምበታል፡፡

16.4. ቦርዱ አስፈላጊና ለአስተዳደር አካላት የስራ አፈጻጸም ጠቃሚ ሆኖ ካላገኘው በስተቀር ስለጉዳዩ በዝርዝር ሳይገባ የአስተዳደር ችሎቱ ወይም የምርት ገበያው በሰጠው ወሳኔ ላይ ድምዳሜወን ብቻ በመግለጽ ወሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

16.5. ቦርዱ የወሳኔወን ትክክለኛ ግልባጭ ለተከራካሪ ወገኖች ይሰጣል፤ ለሚመለከታቸው አካላትም ያስተላልፋል፡፡

16.6. የቦርዱ ወሳኔ የሚጨረሻው የባለስልጣኑ ወሳኔ ይሆናል፡፡ ሆኖም በቦርዱ ወሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን አግባብ ባለው ህግ በተደነገገው ማስረት ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

17. ከችሎት ስለመነሳት፤

17.1. ማንኛወም የቦርድ አባል በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ማስረት በማድረግ፡

/ሀ/ ከተከራካሪ ወገኖች፤ ወይም

/ለ/ በራሱ ተነሳሽነት ከችሎት እንዲነሳ በማቅረብ ጥያቄ፤ የቀረበወን ጉዳይ በዳኝነት እንዳያይ ከችሎት እንዲነሳ ሊወሰን ይችላል፡፡

17.2. አንድ የባለስልጣኑ የቦርድ አባል ከዚህ በታች ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ ሲያጋጥም ከችሎት እንዲነሳ ለመጠየቅ ምክንያት ይሆናል፡፡

/ሀ/ ከተከራካሪው ወገን ወይም ከጠበቃው ጋር የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ወይም ጠብ ያለው እንደሆነ፤

/ለ/ ከተከራካሪው ወገን ወይም ከጠበቃው ጋር በማናቸወም የዳኝነት ወይም የሽምግልና ሚድረክ የተያዘ ጉዳይ ያለው እንደሆነ፤

/ሐ/ በይግባኝ የቀረበወን ጉዳይ በቅድሚያ በግል የሚያውቀወና ምክርም የተጠየቀበት ጉዳይ የሆነ እንደሆነ፤

/መ/ ከዚህ በላይ ከተማከቱት ዉጪ የቦርዱ አባል በዳኝነት ቢሰየም ትክክለኛ ፍትህ አይሰጥም የሚያሰኝ ምክንያት ሲኖር፡፡

18. የቦርድ አባል ከዳኝነት እንዲነሳ ስለማጠየቅና ወሳኔ ስለማስጠት

18.1. ማንኛወም የቦርድ አባል በአንቀጽ 17.2. ስር ከተማለከቱት ወስጥ በይግባኝ የቀረበወን ጉዳይ ከመሜልከት የሚከለክል ምክንያት መኖሩን ሲረዳ ይህንኑ ሁኔታ በጽሁፍ በማስወቅ ራሱን ከዳኝነት ማግለል አለበት፡፡

18.2. አንድ ተከራካሪ ወገን በአንቀጽ 17.2. የተማለከቱት ሁኔታዎች መኖራቸወንና የቦርድ አባሉ ራሱን ከዳኝነት ያላገለለ ሲሆን ይህንኑ ገልጾ አባሉ ከችሎት እንዲነሳለት ሊያማከት ይችላል፡፡

18.3. በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ /1/ የተማለከተው ማሜልከቻ ለቦርዱ ሲቀርብ እንዲነሳ ጥያቄ ከቀረበበት ውጭ ያሉት ሌሎች የቦርድ አባላት የማሜልከቻወን ይዘት ሞምረው አባሉ ከችሎት እንዲነሳ ወይም የቀረበው ምክንያት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ይወስናሉ፡፡

18.4. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ /1/ አባሉ በሚያቀርበው መግለጫ ወይም በንዐስ አንቀጽ /3/ ማስረት ቦርዱ በሚሰጠው ወሳኔ አባሉ የተጓደለበት እንደሆነ ጉዳዩን በቀሩት የቦርዱ አባላት አይቶ ወሳኔ ይሰጣል፡፡

18.5. አንድ የቦርድ አባል ከችሎት እንዲነሳለት የሚያማከት ወገን በማሜልከቻው የገለጸው ሁኔታ በሀሰት ላይ የተማሰረተ ወይም አባሉ ትክክለኛ ዳኝነት ከማስጠት ለማካላከል መሆኑ ሲታመን በጠየቂው ላይ እስከ ብር አምስት መቶ የሚደርስ ቅጣት ሊጣልበት ይችላል፡፡

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

19 የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ይግባኝ የማጠየቅ መብት

ባለሥልጣኑ በራሱ አነሳሽነት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ቦርድ ወሳኔ ላይ የሕግ ስህተት አለ ብሎ ሲያምን ስህተቱ እንዲታረም ይግባኝ ለቦርዱ ለማቅረብ ይችላል፡፡

20 ስለወክልና

ማንኛወም በባለስልጣኑ ቦርድ በይግባኝ ባይነት ወይም በሜልስ ሰጪነት የሚቀርብ ተከራካሪ ስለእርሱ ሆኖ የሚከራከር ጠበቃ ሊያቆም ወይም ጉዳዩን ለማከታተል ሌላ ሰው ህጋዊ ወክልና በማስጠት መወከል ይችላል፡፡

21. አስተርጓሚ ስለመመደብ

21.1. ቦርዱ የዳኝነት ስራወን የሚሠራው በፌደራል መንግስቱ የስራ ቋንቋ ነው፡፡

21.2. በቦርዱ በይግባኝ ባይነት ወይም በሌላ ሰጪነት የሚከራከረው ሰው በቦርዱ የስራ ቋንቋ ሀሳቡን መግለጽ የማይችል መሆኑን ገልጾ ከአስተርጓሚ ጋር ለመቅረብ እንዲፈቀድለት ሲጠይቅ ቦርዱ ይህንኑ ሁኔታ የተረዳ እንደሆነ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

22. የማስቻያ ስፍራ

የቦርዱ የማስቻያ ስፍራ አዲስ አበባ የሚገኘው የባለስልጣኑ ዋና መስሪያቤት ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሚችለውም ሌላ ስፍራ ሊያስችል ይችላል፡፡

23. በግልጽ ችሎት ስለማስቻል

ቦርዱ ለህዝብ ክፍት በሆነ ቦታና ሁኔታ ያስችላል፡፡ ሆኖም በይግባኝ የሚታየው ጉዳይ በግልጽ ችሎት ቢታይ፤

/ሀ/ በህዝብና በመንግስት ሰላምና ጸጥታ፤ ወይም

/ለ/ በተከራካሪ ወገኖች የንግድ ሚስጥርና ሚስጥራዊ ዝና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል ተብሎ ሲታመን ቦርዱ ጉዳዩ በዝግ ችሎት እንዲታይ ሊወስን ይችላል፡፡

24. የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርአት ሕግን ስለማጠቀም

ቦርዱ በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ የሥነ-ሥርዓት ጉዳዮች ሲያጋጥሙት አግባብነት ያላቸውን የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎች ሊከተል ይችላል፡፡

**25. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

<u>**ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በቦርዱ በመታየት ላይ የሚገኙ ጉዳዮች ክርክር በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት የሚታይ ይሆናል፡፡**</u>

**26. <u>ስለማሻሻል</u>**

<u>**ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ በሙሉ ወይም በከፊል ሊያሻሽለው ይችላል፡፡**</u>

**27. <u>መመሪያው ተፈፃሚ ስለሚሆንበት ጊዜ</u>**

<u>**ይህ መመሪያ ከሀምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡**</u>

<u>**የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ቦርድ ሰብሳቢ**</u>